670/2013

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በትራንስፖርት ሚኒስቴር
የትራንስፖርት ባለሥልጣን
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport
Transport Authority

ቁጥር ትገ/ ዋዳ/ 160/08
No.
ቀን 10/2/08 ሺ፱
Date 200

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ለተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት
**ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

ጉዳዩ:- **የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው ተሽከርካሪን ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የወጣውን መመሪያን ይመለከታል**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 እና በመ/ቤታችንም በኩል የሚጠበቅብን ተግባርና ኃላፊነት በግልፅ ለመወሰን እንዲያስችለን መመሪያ ቁጥር 12/2007 ዓ.ም ወጥቶዋል፡፡

ስለሆነም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከው የመመሪያው ኮፒ 13 ገጽ፣ በመሥሪያ ቤታችን የተዘጋጀው መመሪያ 4 ገጽ ኦርጅናል እና ከቀረጥና ታክስ ነጻ በሚገባው ተሽከርካሪ መለያ ልዩ ሰሌዳ የሚመረትበት አለም አቀፍ የሆነውን ልዩ ምልክት 1 ገጽ ኦርጅናል ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከላችሁ ሲሆን ለሚመለከተው አካል መመሪዎች እንዲደርሱ በማድረግ እንድትፈጽሙና እንድታስፈጽሙ እያስታወቅሁ የመ/ቤታችን የሠሌዳና ምልክቶች ምርት ሥርጭት የሥራ ሂደትም ብዛቱን ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ለግል አገልግሎት የሚውል ልዩ ምልክትን ያለው ሰሌዳ እንድታዘጋጁ እያሳሰብኩ ለግንዘቤ እንዲረዳችሁ ከላይ የተጠቀሱትን መመሪያዎችና ልዩ ምልክት እንዲደርሳችሁ ተደርጓል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

**ግልባጭ:-**
ለሠሌዳና ምልክቶች ምርት ሥርጭት የሥራ ሂደት
**ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

# በትራንስፖርት ሚኒስቴር
# የትራንስፖርት ባለሥልጣን

## የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው ተሽከርካሪን ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 670/2013

የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

2008 ዓ.ም

## የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው ተሽከርካሪን ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 12/2007

### መግቢያ

የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው አካል ጉዳተኞች በተሽከርካሪ በመታገዝ ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተገቢውን ተሳትፎ ለማድረግ እንዲችሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 መሰረት ለአካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ አገር ውስጥ የሚገቡበትና የሚመዘገቡበት በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7(2) ቀ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ ባለስልጣኑ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአካል ጉዳተኞችን ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገቢያ ፈቃድ የሚያገኙበትና የሚመዘገቡበት እንዲሁም በመንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ ምቹ ለማድረግ የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 670/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ ካላሰጠው በቀር ከገንዘብና ኢኮኖሚ ሚንስቴር የተላለፈው መመሪያ ቁጥር 41/2007 የተሰጡት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በተጨማሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሚከተለው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡

1. ልዩ ምልክት ማለት በአለም አቀፍ ደረጃ ለአካል ጉዳተኛ ልዩ ምልክት ሆኖ የዊልቸር ምልክት ያለበት ነው፡፡
2. ባለስልጣን ማለት በአዋጅ ቁጥር 468/1997 የተቋቋመው ትራንስፖርት ባለስልጣን ነው፡፡
3. አግባብነት ያለው መዝጋቢ አካል ማለት ተሽከርካሪዎችን የመመዝገብ ሥልጣን ወይም ውክልና ያለው ተቋም ማለት ነው፡፡
4. ተቆጣጣሪ አካል ማለት ተሽከርካሪዎችን ለመቆጣጠር ሥልጣን ያለው የመንግስት አካል ነው፡፡

የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

የትራንስፖርት ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 681/2002 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውንም የመንቀሳቀስ ችግር ላለበት ለአካል ጉዳተኛ ተብሎ በገንዘብና በኤኮኖሚ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 41/2007 መስፈርት አሟልቶ ሀገር ውስጥ ለሚገቡና ለገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>አላማ</u>

1. የዚህ መመሪያ አላማ የተሽከርካሪ መዘጋቢ ለአካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪን በዚህ መመሪያና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር በመመሪያ ቁጥር 41/2007 የተላለፈውን ተግባራዊ .ለማድረግና፤

2. የአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ በልዩ ምልክት አማካኝነት ተቆጣጣሪ አካላት ድጋፍና ትብብር እንዲደረግላቸው ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የተለያዩ አካላት ኃላፊነትና ተግባር</u>

5. <u>ትራንስፖርት ሥልጣንና ተግባርና ኃላፊነት</u>

   1. ለአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪዎች ማስገቢያ ፈቃድ የሚሰጠው በገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር የተሰጠውን ከቀረጥ ነጻ የሆነ ለአንድ ተሽከርካሪ የሚያገለግል 1600 ሲ.ሲ. የማይበልጥ ተሽከርካሪ ለ6 ወር የሚያገለግል ፈቃድ ባለስልጣኑ ይሰጣል፡፡
   2. ሀገር ውስጥ ገብቶ ምዝገባ የተካሄደው የአካል ጉዳተኞች ተሽከርካሪዎች ከመዝጋቢው አካል የተላለፉለትን መረጃን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴርና ለሠራኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር በየአመቱ መረጃው ያስተላልፋል፡፡
   3. ከቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው ግለሰቦች የሚጠቀሙበት የዊልቸር ምልክት ያለበትን ሠሌዳ ያመርታል ያሰራጫል ፤
   4. የአካል ጉዳተኞች መንጃ ፈቃድ አሰጣጥና አሰለጣጠን በተመለከተ ሰርኩላር ያስተላልፋል፡፡

6. <u>የቀረጥና ታክስ ነፃ ባለመብት ኃላፊነትና ተግባር</u>

   1. ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ ምዝገባ በማካሄድ አግባብነት ካለው አካል የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ሳይኖረው እና የዊልቸር ምልክት የለበትን ሰሌዳ ሳይለጥፍ መንገድ ላይ መንቀሳቀስ የለበትም ፤
   2. ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ተሽከርካሪውን በሚመለከት አግባብ ላለው አካል የሚቀርብ ምዝገባና የባለቤትነት መታወቂያን ደብተር ማመልከቻ ለተሽከርካሪው



አዲስ አበባ

ዋና ዳይሬክተር

ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠ የቀረጥና ታክስ ነፃ ፈቃድ ማስገቢያ እና የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ጋር ተያይዞ መቅረብ እና፣

3. ተሽከርካሪው በመንገድ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ኦርጅናልና ኮፒ ሊብሬ በመኪና ውስጥ መያዝ አለበት ፡፡

7. <u>አግባብነት ያለው የምዝገባ አካል ኃላፊነትና ተግባር</u>

1. ለአካል ጉዳተኞች ሀገር ውስጥ የገቡ ተሽከርካሪዎች መመሪያ ቁጥር 41/2007 እና በዚህ መመሪያ መሰረት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል የሚከተሉትን የተሽከርካሪ ዝርዝር መግለጫ ያስቀምጣል፡-
   - ሀ. የባለንብረት ስምና አድራሻ፣
   - ለ. የሻንሲ ቁጥርና የሞተር ቁጥር፣
   - ሐ. የሞተር ጉልበትና የምርት ዘመን፣
   - መ. ቀለሙን፣
   - ሰ. የአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪው ከቀረጥ ነፃ የገባ መሆኑን በሊብሬ ላይ በመግለፅ የውልቸር ምልክት ያለበትን ሠሌዳ ይሰጣል፣
2. መዝጋቢው አግባብነት ያለው አካል ለአካል ጉዳተኞች የመዘገባቸውን ተሽከርካሪዎችን በየ6 ወሩ ለባለስልጣኑ ሙሉ መረጃ ማስተላለፍ እና፣
3. ለአካል ጉዳተኞች የሚዘጋጀው ሰሌዳ ፍላጎት በየጊዜው ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

8. <u>የተቆጣጣሪ አካላት ኃላፊነትና ተግባር</u>

የመንገድ ደህንነት ተቆጣጣሪ አካላት የዊልቸር ምልክት አድርጎ የሚንቀሳቀሰውን ተሽከርካሪ በትራፊክ መብራት ላይ ፣ በማቆሚያ ቦታ ላይና በማንኛውም የጉዞ መስመር ላይ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

9. <u>የተከለከሉ ተግባሮች</u>

ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ ለራሱ፣ለቤተሰቡ ለስራ እንቅስቃሴና ከግላዊ አገልግሎት በሰተቀር ለንግድና ለኪራይ መጠቀም አይችልም፣

## <u>ክፍል ሦሥት</u>

10. <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

1. ልዩ ምልክት ሰማያዊ መደብ ባለው ክብ ውስጥ ነጭ የዊልቸር ምልክት ያለበት ሰሌዳ ማንኛውም ተቆጣጣሪ አካል ትብብር ማድረግ አለበት፡፡
2. ማንኛውም አካል ጉዳተኛ ከዚህ መመሪያ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 መሰረት ልዩ ምልክት ሰሌዳ ለጥፎ ማሽከርከር ይኖርበታል፡፡

3. የአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ ተጠቃሚው ባለፉት አስር አመታት ጊዜ ውስጥ በስሙ የግል ተሽከርካሪ እና ከቀረጥ ነፃ ያላስገባ መሆን አለበት፡፡
4. የአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 12/2007 ከአዋጅ ቁጥር 681/2002 ስለተሽከርካሪ መለያ መመርመሪያና መመዝገቢያ የወጣውን አዋጅ እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 41/2007 እንዲሁም የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የስራ ሂደት የአሰራር መመሪያ ቁጥር 2 መሰረት ተጣጥም ተፈጻሚ ይሆናል፣
5. በልዩ ሁኔታ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ በመቅረብ ሰነዶችን በማሟላት የባለቤትነት ማረጋገጫ መውሰድና በየዓመቱም በአካል በመቅረብ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 11.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ----------------------------------ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ካሣሁን ኃ/ማርያም
የትራንስፖረት ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንቅስቃሴ ትኩረት ይደረግ

ራዳ ባርነን
Rädda Barnen

ኢአጉብማ
ENAPH

የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ